# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ሁርሶ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ

በለጥሻቸው ልዑልሰገድ

የሁርሶ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በ2008 ዓ.ም ተገንብቶ ወደ ሥራ የገባ ጣቢያ ነው ። ድሬዳዋ ቁጥር-1 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ላይ እያንዳንዳቸው 131 ነጥብ አምስት ኪሎ ቪልት የሚይዙ ሁለት ትራንስፎርመሮች አሉት ። ድሬዳዋ ቁጥር-3 ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ላይ ደግሞ እያንዳንዳቸው 63 ሜጋ ቮልት አምፒር (MVA) የሆኑ ሁለት አውቶ - ትራንስፎርመሮች አሉ ። እነዚህ ሁለት አውቶ-ትራንስፎርመሮች ተጠቃሚዎች እየበዙ በመምጣታቸውና ትራንስ ፎርመሮቹ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን ጫና በመሸከሙ ምክንያት ይህንን ጫና ለመቀነስ እና ይል ተደራሽ እንዲሆን የሁርሶ ማከፋፈያ ጣቢያ እንዲገነባ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሁርሶ ማከፋፈያ ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን ሞገስ እንደሚገልጹት፤ በጣቢያው ሁለት ባለ 230 ኪሎ ቮልት ገቢ መስመር ያለ ሲሆን ፤ ገቢ መስመሮቹ ከቆቃ-1 እና ከቆቃ-2 የሚመጡ ናቸው ። አሁን ላይ ከቆቃ-1 የሚመጣ መስመር ብቻ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። የሆነበት ምክንያት ሁለቱም ገቢ መስመሮች ጥቅም ላይ ከዋሉ ቮልቴጁ ከፍተኛ ስለሚሆን ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ደንበኛ እስከሚገኝ ድረስ ለጊዜው አንድ ገቢ መስመር ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉን አስታውቀዋል ።




አቶ ሰለሞን ሞገስ፣

እንደ እርሳቸው ገለጻ ፣ ጣቢያው በ230 ኪሎ ቮልት አምስት ወጪ መስመሮች አሉት ። እነሱም አዲጋላ (ጅቡቲ)፣ አይሻ፣ ድሬዳዋ ቁጥር-3 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ መስመር1፣ ድሬዳዋ ቁጥር-3 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ መስመር -2 እና ሁርሶ የባቡር መስመር እንዲሁም የ132 ኪሎ ቮልት ሁለት ወጪ መስመር ያለው ወደ ሐረር እና ጎታ የተዘረጉ ናቸው።

ከዚህ ባሻገር ጣቢያው ሦስት ባለ33 ኪሎ ቮልት አነስተኛ ወጪ መስመሮች መኖራቸውን የሚናገሩት አቶ ሰለሞን፤ እነዚህም ኢንዱስትሪ አንድና ሁለት እንዲሁም ከጣቢያው 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ኤረር ከተማ 33 ኪሎ ቮልት ወጪ መስመር አለ። ጣቢያው 15 ሺህ ኪሎ ቮልት አንድ ወጪ መስመር ያለው ሲሆን ይህ ወጪ መስመር ሙሉ ለሙሉ በሁርሶ ለሚገኘው ወታደራዊ ማሰልጠና ማዕከል እና ለሁርሶ ከተማ የሚያገለግል ወጪ መስመር መሆኑንም አብራርተዋል ።

ዘመኑ የቴክኖሎጂ እና የኢንዱስትሪ እንደመሆኑ መጠን ያለ ኤሌክትሪክ ምንም ነገር መስራት አይቻልም። ይህ ጣቢያ በምሥራቅ ሪጅን ግዙፉ እና ዋናው ማከፋፈያ ጣቢያ ነው። ድሬዳዋ ከተማ ላይ እየተስፋፉ ላሉ ኢንዱስትሪዎች ለኢትዮ - ጅቡቲ የባቡር መስመር በበቂ ሁኔታ ኃይል ተደራሽ እንዲሆን እያደረገ ይገኛል። ለማህበረሰቡም ቢሆን በቂ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ እንዲሆን ይህ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠ ነው።

በጣቢያው የበዓላት ቀንን ጨምሮ በየቀኑ ለ24 ሰዓት ያለማቋረጥ የኦፕሬሽን ሥራ ይሰራል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በዚህ የኦፕሬሽን ሥራ ውስጥ በየቀኑ ያሉ መረጃዎች የሚመዘገቡ ሲሆን ቀላል እና በጣቢያው ሰራተኞች አቅም መፈታት የሚችሉ የኤሌክትሪክ ችግሮች ሲኖር በጣቢያው የውስጥ አቅም እንዲስተካከሉ እንደሚደረግ አመልክተዋል። ከጣቢያው አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች በሚገጥሙ ጊዜያት ደግሞ ለሚመለከተው አካል በፍጥነት ሪፖርት በማድረግ አስቸኳይ ጥገና እንዲካሄድ የሚደረግ መሆኑን ጠቁመዋል ።

ከዚህ በተጨማሪ የጣቢያው አንዱ ወጪ መስመር በአዲጋላ የማከፋፈያ ጣቢያ በኩል ወደ ጅቡቲ የሚሄደው መሆኑን ገልጸው፤ ይህ መስመር የኤሌክትሪክ ኃይል ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ በማምጣት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ የሚገኝ ስለመሆኑም ተናግረዋል። አቶ ሰለሞን ፣ ወደ ጅቡቲ የሚሄድ ወጭ መስመር 120 ሜጋ ዋት ብቻውን መሸከም የሚችል ሲሆን በዓመት ብዙ ሚሊዮን ዶላሮችን ገቢ ማምጣት የሚችል ነው። ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገርም በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲጠናከርም የራሱን ሚና እንደሚጫወትም አመልክተዋል።

በመጨረሻም ፣ የሁርሶ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በዚህ አካባቢ መገንባቱ ሳይቆራረጥ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማህበረሰቡ እንዲደርስ አድርጓል። ማህበረሰቡም ለኃይል ፍጆታ የሚጠቀመው የኤሌክትሪክ ኃይል በመሆኑ ዛፎችን በመቁረጥ ለኃይል ፍጆታ በማዋል የሚመጣውን የአየር መበከል ከመከላከል አንፃር ከፍተኛ ሚና አለው። ከዚህ ባሻገር ይህ ጣቢያ በዚህ አካባቢ በመገንባቱ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ እድል እንዲፈጠር አድርጓል። ከጥበቃ ጀምሮ እስከ ኦፕሬሽን ስራዎች ድረስ ማህበረሰቡን በማሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የቻለ ጣቢያም ነው ሲሉ አክለው ተናግረዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ